| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | "በፍጹም ፡ ድል ፣ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ እንሸጋገር ። " |
| ደሁሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ታኅሣሥ ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፣ ቍ.2014-002 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## በፍጹም ፡ ድል ፣ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ እንሸጋገር ።




ወቀቱ ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፡ ነው ፤ በጦር ፡ ምጋቤ [1] ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ [2] ፣ ዐዲስ ፡ የተቋቋመው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዘመናዊ ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ እየተቈጣጠረ ፡ ሰላሙን ፡ ያረጋጋል ። የፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ ተፈትቶ ፣ እዚህም ፡ እዚያም ፡ የሚያውኩ ፡ ጥቂት ፡ ርዝራዦች ፡ ሲታዩ ፣ ቍጥር ፡ ጦር ፡ በእያሉበት ፡ እየተላከ ፣ በቀላሉ ፡ ተደምስሰዋል ። ጐንደር ፡ ላይ ፡ የመሸገው ፡ የጄኔራል ፡ ናዚ ፡ ጦር ፡ ግን ፣ ለረዥም ፡ ጊዜ ፡ ባካበተው ፡ ሥንቅና ፡ ትጥቅ ፤ ባስሰለፈው ፡ ሰራዊት ፡ ብዛት ፡ ተማምኖ ፦ "ብቻዬን ፡ እወጣዋለኹ" ፡ በሚል ፡ ከንቱ ፡ ተስፈኝነት ፡ አሻፈረኝ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፣ የዘመቻ ፡ ትእዛዝ ፡ የተሰጠው ፡ በደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነኽ ፡ የሚመራው ፡ ቍጥር ፡ ጦር ፣ ባስደናቂ ፡ ዥግንነትና ፡ ስልት ፡ የጐንደርን ፡ ምሽግ ፡ ሰብሮ ፡ በመግባት ፣ ኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፡ የዐምስት ፡ ዓመቱን ፡ ጦርነት ፡ መደምደሚያ ፡ ድል ፡ አበሠረ ።



ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡ በላይነኽ ፡ እና ፡ ሰራዊታቸው ።

ታሪክ ፣ እየተተባተበም ፡ ቢኾን ፣ ራሱን ፡ ይደግማል ፡ ይባላል ። ዛሬ ፣ በሰማንያኛ ፡ ዓመቱ ፣ በተመሳሳይ ፡ ኹኔታ ፣ አንበሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊና ፡ ሕዝባዊ ፡ ሰራዊት ፡ ፋኖ ፣ የምናውቀውን ፡ የፋሺዝም ፡ የቀን ፡ ዥብ ፡ አከርካሪውን ፡ በክርኑ ፡ ሰብሮታል ፤ አፉን ፡ ግን ፡ ገና ፡ አላስዘጋውም ። የኹለቱ ፡ ታሪካውያን ፡ ድርሶች ፡ መመሳሰል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ያበቃል ። ዛሬ ፣ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እና ፡ አስመራ ፡ ያደባው ፡ የሌሊት ፡ ዥብ ፡ ገና ፡ አልተነካምና ፣ ድሉ ፡ ፍጹም ፡ ኾኖ ፡ አልተከናወነም ፤ እንዲያውም ፡ እንዳይቀለበስ ፡ ያሠጋል ።

ርግጥ ፡ ነው ፣ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነቅቷል ። **ለምልክዮሽ** ፡ (ለ"ኢምፔሪያሊዝም") ፡ ኀይሎች ፡ ባደሩ ፡ በራሱ ፡ ልጆች ፡ ተደጋግሞ ፡ የተከዳበት ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ታሪኩ ፡ የማይረሳውን ፡ መሪር ፡ ትምህርት ፡ አስተምሮ ፡ አብስሎታል ። ከራሱ ፡ እና ፡ ከሚያመልከው ፡ አንድ ፡ አምላኩ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ መድኀኒት ፡ እንደሌለው ፡ ዐውቋል ። ምልክዮሽ ፡ የደገሰለት ፡ የጥፋት ፡ "Plan-A" ፡ ኅዳር ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ፣ ነፍሳቸውን ፡ ይማርና ፣ በዥግናው ፡ ዐበረ ፡ አዳሙ ፡ አስተባባሪነት ፡ በዘመተው ፡ ሀገራዊና ፡ ሕዝባዊ ፡ ሰራዊት ፣ ባጪር ፡ ከሽፏል ። "Plan-B" ፡ ቀጠለ ፤ ክፉኛ ፡ የተደመሰሰውን ፡ ወያኔ ፡ ዳግም ፡ እንዲያንሰራራ ፣ በዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ አገዛዝና ፡ በዓለም ፡ የርዳታ ፡ ድርጅቶች ፡ አማካይነት ፣ ምልክዮሽ ፡ ለስምንት ፡ ወራት ፡ አስታምሞ ፡ ከቀለበውና ፡ ካስታጠቀው ፡ በኋላ ፣ በተለመደው ፡ ዐቅዱ ፣ ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ኹለት ፡ ወፍ ፡ ለመግደል ፣ ለብዝበዛ ፡ ዐላማው ፡ የማይታለፍ ፡ መሰናክል ፡ የኾነበትን ፡

1 **ምጋቤ** ፤ "ሚኒስቴር" ።

2 **ሲ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ** ፡ (1910-2000 ፡ ዓ.ም.) ፣ የኢ..ሀ.ሥ.አ. ፡ መሥራችና ፡ የቀድሞ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ።


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፣ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐማራን ፡ ለማድቀቅ ፡ ሲል ፥ የጦር ፡ ዐውድማውን ፡ ከ"ትግራይ ፡ ክልል" ፡ ወደ ፡ "ዐማራ ፡ ክልል" ፡ አመጣው ። በንኅለተኛ ፡ (በ"ኒኂሊስት") ፡ ስብከት ፡ ከእምነቱና ፡ ከባህሉ ፡ የተናቀለውን ፡ የ"ትግራይ ፡ ክልል" ፡ ወጣት ፡ አስገድዶ ፡ በማስሰለፍ ፦ "የቻልከውን ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ግደል ፤ ያቅምኽን ፡ ያኽል ፡ ንብረት ፡ ዝረፍ ፤ የቀረውን ፡ አውድመው" ፡ በሚል ፡ የጥፋት ፡ መመሪያ ፡ አዘመተበት ። በታሪክ ፡ ያልታየ ፣ ያልተሰማ ፥ አስሠቃቂ ፣ አስጸያፊና ፡ አስነዋሪ ፡ ድርጊት ፡ ተፈጸመ ። ላለፉት ፡ 30 ፡ ዓመታት ፡ ተመሳሳይ ፡ ፀረ ፡ ሀገራዊ/ፀረ ፡ ዐማራ ፡ ጭፍጨፋዎች ፡ በእየ"ክልሉ" ፡ ሳያቋርጡ ፡ ተፈጽመዋል ። ዋነኛ ፡ ዐላማቸው ፥ ማኅበረሰቦችን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዳይታረቁ ፡ አድርጎ ፡ አጣልቶና ፡ ደም ፡ አቃብቶ ፥ ክልሎቻቸውን ፡ ነጣጥሎ ፡ በ"ሪፓብሊክነት" ፡ ማዋቀርና ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ ዩጎስላቭያ ፡ ማፈራረስ ፡ ነው ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ሀገራዊውን ፡ ሕዝብ ፥ ዐማራን ፥ በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ አንዳች ፡ ድርሻ ፡ እንዳይኖረውና ፡ "ከጨዋታ ፡ ውጭ" ፡ እንዲኾን ፥ "የዝርባ ፡ ዐጥንቱን" ፡ ለመስበርም ፡ ተሞክሯል ። አፈ ፡ ዘርጣው ፡ የወያኔ ፡ ወሬኛ ፥ በሸዋ ፡ ፋኖ ፡ ሽንፈትን ፡ በተከናነበ ፡ ማግስት ፥ ሳት ፡ ብሎት ፡ እንደዘረገፈው ፦ "እኛ ፡ ዐቢይን ፡ አይደለም ፡ የምንፈልገው ፤ የጠላታችንን ፡ [የዐማራን] ፡ አከርካሪ ፡ ሰብረነዋል" ፡ ሲል ፡ የምልክዮሽን ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ምኞትና ፡ መዛለቂያ ፡ ዐቅድ ፡ በድምፅ ፡ ማጕሊያነት ፡ ተናግሮታል ።

"ዐዲስ ፡ አበባን ፡ የወያኔ ፡ እና ፡ የኦ.ነ.ግ. ፡ ጦሮች ፡ ከበዋታል" ፡ የሚለው ፡ የምልክዮሽ ፡ ማዘናጊያ ፥ "ስልታዊ ፡ ማፈግፈግ" ፡ የሚለው ፡ የመንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድም ፡ አፈ ፡ ጮሌነት ፥ በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚፈጸመውን ፡ "የዐማራን ፡ አከርካሪ ፡ የመስበር" ፡ ዐቅድ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ የክዳት ፡ ድርጊቶች ፡ ነበሩ ። ምልክዮሽን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይለት ፤ ወያኔን ፡ ጨምሮ ፥ መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ እና ፡ ግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ ግን ፥ ጊዜውን ፡ ጠብቀው ፥ በሀገር ፡ ክዳት ፡ ወንጀል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይጠየቃሉ ።

የኾነው ፡ ኾኖ ፥ ዝግናው ፡ ሀገራዊ ፡ እና ፡ ሕዝባዊ ፡ ሰራዊት ፡ ፋኖ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ በማረከው ፡ ጠመንጃና ፡ ጥይት ፡ ይህን ፡ የፋሺዝም ፡ የኽርብ ፡ መንጋ ፡ አርበድብዶ ፡ አይቀጡ ፡ ቅጣት ፡ ሲቀጣው ፥ "Plan-B"ም ፡ ዒላማውን ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ሳያሳካ ፡ ከሸፈ ። የዕቅዱ ፡ ክስረት ፡ ቀድሞ ፡ የታየውና ፡ ለጊዜው ፡ የተደናገረው ፡ ምልክዮሽ ፥ በመጨረሻ ፡ ደቂቃና ፡ በችኰላ ፡ በተቀናበረ ፡ "Plan-C" ፥ መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድን ፡ "ወደጦር ፡ ግንባር" ፡ በመላክ ፥ "የበሬን ፡ ውለታ ፡ አህያ ፡ ወሰደች" ፡ እንደተባለው ፥ "የድሉ ፡ ምክንያት" ፡ ኾኖ ፡ እንዲቀርብ ፡ ተደረገ ፤ ... ፡ የተፈለገው ፡ የሀገር ፡ ጥፋት ፡ ከደረሰ ፡ ወዲያ ፥ ... ፡ በመቶ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብ ፡ ካለቀ ፡ ወዲያ ፥ ... ፡ ቤት ፡ ንብረት ፡ ከተዘረፈ ፡ ወዲያ ፥ ... ፡ መሠረተ ፡ ልማት ፡ ከወደመ ፡ ወዲያ ፥ ... ።

የዐማራን ፡ አከርካሪ ፡ ግን ፡ እንኳን ፡ ሊሰብሩትና ፥ አልነኩትም ። በሠኔ ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ፡ በመኻል ፣ በደቡብና ፡ በምሥራቅ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በደረሰው ፡ ዐይነት ፥ የጠፋው ፡ የማይተካ ፡ የንጹሐን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤ የተመዘበረው ፡ የንጹሓን ፡ ድኾች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ንብረት ፡ ነው ፤ የወደመው ፡ የሀገር ፡ ሀብት ፡ ነው ። "ተከናንበው ፡ ቢተኙ ፥ ገልጦ ፡ የሚወጋ ፡ አምላክ ፡ አለ" ፤ "በቀል ፡ የኔ ፡ ነው" ፡ ያለ ፡ የየዋሃን ፡ ተበቃይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ አኹንም ፡ ይበቀላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተከድቶ ፡ በተከዘበት ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፥ "የምጣዱ ፡ ሳለ ፥ የዕንቅቡ ፡ ተንጣጣ" ፡ ኾኖ ፥ በምዕራቡ ፡ ዓለም ፥ ምልክዮሽ ፡ መልምሎ ፡ ባደራጃቸው ፡ ወኪሎቹ ፡ አማካይነት ፡ ተቀስቅሰው ፡ የተነዱ ፡ እልፍ ፡ አእላፍ ፡ የዋሃን ፡ "ዲያስፖራዎች" ፥ የዐቢይንና ፡ የኢሳይያስን ፡ ጨቋኝ ፡ መንደር ፡ ገነንነትና ፡ የምልክዮሽ ፡ የ"ትሮይ" ፡ ፈረስነታቸውን ፡ ዘንግተውት ፥ በድጋፍ ፡ ሰልፍ ፡ የዓለም ፡ መዲናዎችን ፡ አጨናንቀው ፡ ከረሙ ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ሰልፍ ፡ የወጣው ፥ በኢትዮጵያ ፡ አንጻር ፥ የምዕራባውያንን ፡ የጠላትነት ፡ ድርጊት ፡ በደረቁ ፡ በመቃወም ፥ "በቃ!" ፡ ለማለት ፡ ነው ። በሰፊው ፡ የተነዛውና ፡ በይፋ ፡ የተወራኘው ፡ የምዕራባውያን ፡ ፀረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስልታዊ ፡ አቋም ፥ ለጭፍሮቻቸው ፡ ዐቢይና ፡ ኢሳይያስ ፡ ሕዝባዊ ፡ ድጋፍን ፡ ለማስገኘት ፡ መኾኑን ፡ የተረዳው ፡ ጥቂት ፡ ሰው ፡ ነው ። የእነዚህን ፡ መንደር ፡ ገነኖች ፡ ይዘት [3] ፡ መደገፍ ፥ በምንም ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ተገቢነት ፡ አይኖረውም ፤ በጨዋነት ፡ ብቻ ፥ "የዋህነት ፡ ነው" ፡ ብለን ፡ እናልፈዋለን ። "ኢትዮጵያን ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ሰጥተናታል" ፡ ያሉት ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ አልነበሩምን ፧ ኦነግ-ሸኔን ፡ ያሠለጠነው ፣ ያስታጠቀውና ፦ "ኢሰብአዊነት ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ ነው" ፡ ብሎ ፡ ያስጠናው ፡ ሻዕቢያ ፡ አይደለምን ፧ ኦነግ-ሸኔ ፡ ከእነሙሉ ፡ ትጥቁ ፡ ከሻዕቢያ ፡ የጦር ፡ ሰፈሮች ፡ ወጥቶ ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስሠቃቂዎች ፡ ግድያዎቹን ፡ አላንዳች ፡ ተጠያቂነት ፡ እንዲፈጽማቸው ፡ የፈቀዱ ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አይደሉምን ፧

3 **ይዘት** ፤ በግእዝ ፡ 'እኀዘት' ፥ አለሥልጣኑ ፥ መንግሥታዊ ፡ ኀይልን ፡ በእጁ ፡ መናኛ ፡ የጨበጠ ፡ የመንደር ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ ("régime") ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

ምክትላቸው ፡ "ኢትዮጵያዊነት ፡ ሱስ ፡ ነው" ፡ ሲሉን ፥ ይህን ፡ ያሉት ፡ ከትምህርት ፡ ማነስ ፡ ይኾናል ፡ ብለን ፡ ነበር ፤ አለቃቸው ፡ ጨምረው ፡ "... ፡ ስንሞት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ነን" ፡ ሲሉ ፥ የጠረጠርነውን ፡ ከይሲነት ፡ አረጋገጡልን ። ቀጥለውም ፥ ችግኙን ፡ ዐፈር ፡ እያለበሱ ፡ "ኢትዮጵያን ፡ እናልብሳት" ፡ ዐሉን ። መጽሐፋቸውንም ፡ "መደመር" ፡ ዐሉት ፤ የ"ደመረ"ን ፡ ትርጕምም ፡ አለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድንና ፡ አለቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌን ፡ ጠቅሰው ፡ ዐተቱልን ፤ መልካም ፡ ነው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ዐማርኛ ፡ ነው ፤ ፊደል ፡ የቈጠረ ፡ ኹሉ ፡ ይገባዋል ። ንባብ ፡ የዠመሩት ፡ ቁርኣንን ፡ በመቅራት ፡ ነውና ፥ "ዐረብኛውስ ፡ ምን ፡ ይላል ፧ " ፡ ብለን ፡ ጠየቅን ። "ደመረ — دمر " ፡ ፈረሰ ፡ ማለቱን ፡ አገኘን ። በእውነቱ ፥ ሌላ ፡ ሰውን ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ባልተመራመርን ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ከወጡበት ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፡ ፀረ ፡ ሀገራዊ / ፀረ ፡ ዐማራ ፡ ጥቃት ፡ በ"መንግሥት" ፡ አካላት ፡ አነሣሽነትና ፡ ድጋፍ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ ሲፈጸም ፥ መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንዳች ፡ የዕርምት ፡ ርምጃን ፡ መፈጸም ፡ ቀርቶ ፥ የሐዘን ፡ መግለጫንም ፡ እንኳ ፡ አላወጡ ፥ የተጐዱትን ፡ አልጐበኙና ፡ አላጽናኑ ። አንድም ፡ የ"ክልል" ፡ ኀላፊ ፡ ኾነ ፡ የጸጥታ ፡ ኀይል ፡ አዛዥ ፡ አልተሻረ ፡ ወይ ፡ በሕግ ፡ አልተጠየቀ ። የዐሩሲውን ፡ ጳጳስ ፡ ተከትለው ፥ ርሳቸውም ፡— "ምን ፡ እንዳታመጡ ፧ " ፡ ዐሉን ። "ካስፈለገ ፥ ወደ ፡ ጥፍር ፡ መንቀል ፡ መመለስ ፡ አያቅተንም" ፡ ብለው ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ በዛቱትም ፡ መሠረት ፥ እንሆ ፥ ሰሞኑን ፡ መዜንዎችን ፡ መሸበቡንና ፡ ማሰሩን ፡ አጠናክረዋል ።

ይህን ፡ በምናስታውስበት ፡ በዚህ ፡ ቅጽበት ፥ ንጹሓን ፡ በወለጋ ፡ እና ፡ በምዕራብ ፡ ጐዣም ፣ በኢሉባቦር ፡ እና ፡ በከፋ ፣ በሸዋ ፡ እና ፡ በወሎ ፡ እንደሚታረዱ ፡ አንዘንጋ ።

ወደድጋፍ ፡ ሰልፉ ፡ ስንመለስ ፥ "ሕዝብ ፡ በዴሞክራሲያዊ ፡ መንገድ ፡ የመረጠውን ፡ መንግሥት ፡ ምዕራባውያን ፡ በምን ፡ አገባብ ፡ ነው ፡ አናውቅኽም ፡ የሚሉት ፧ " ፡ እያሉ ፡ ትውልደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የ"ESAT ፡ ጋዜጠኞች" ፡ እና ፡ አለቆቻቸው ፡ ከዐዲስ ፡ አበባ ፡ እና ፡ ከምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ ዘንቀውና ፡ ቀላቅለው ፡ የነዙት ፡ የሐሰት ፡ ስብከት ፡ ግን ፥ ፈጽሞ ፡ ተቀባይነት ፡ የለውም ። ይህ ፡ ድርጊት ፡ የ"ESAT"ን ፡ የቅጥረኝነት ፡ ሐሜት ፡ በማያጠራጥር ፡ ኹኔታ ፡ አጠናክሮበታል ። ከቶ ፡ በየትኛው ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ በ"ዴሞክራሲያዊ" ፡ ምርጫ ፡ አንድ ፡ ፓርቲ ፡ 98% ፡ መቀመጫዎችን ፡ የሚቈጣጠረው ፧ ወይስ ፡ ሙሶሊኒም ፣ ሂትለርም ፣ መለስ ፡ ዜናዊም ፡ "እንደተመረጡ" ፡ ኹሉ ፥ ዐቢይም ፡ ተመርጧል ፡ ለማለት ፡ ይኾን ፧ የESAT ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ መራቀቅ ፡ አይጠይቅምና ፥ እንተወው ።

ከዐዲስ ፡ አበባ ፡ "ወደጦር ፡ ግንባር" ፡ መለስ ፡ ቀለስ ፡ የሚሉት ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፥ መራራውን ፡ ዜና ፡ በቅርቡ ፡ ሊያረዱን ፡ ይዘጋጃሉ ። የኢትዮጵያ ፡ ጥርየት ፡ ("ኤኮኖሚ") ፡ ወድሟል ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ያለ ፡ የሌለ ፡ ሀብቱን ፡ ለጦርነት ፡ አውሎ ፥ ካዝናው ፡ ባዶ ፡ ኾኗል ። መንደር ፡ ገነን ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፥ መስከረም ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ፥ ዐዲስ ፡ "ለተመረጠው" ፡ የተወካዮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ባደረጉት ፡ ንግግር ፡ በጨረፍታ ፡ የገለጹትን ፡ የ"Sovereign Fund" ፡ ጕዳይ ፡ በመተንተን ፥ ለውጭ ፡ ባለሀብቶች ፡ (ለምዕራባውያን!) ፡ የሚቸበቸቡትን ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ዝርዝር ፡ እና ፡ የሚገኘውን ፡ ዶላር ፡ ይፋ ፡ ያደርጋሉ ። አኹንም ፥ "ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ኹለት ፡ ወፍ ፡ ..." ፤ ተጠቃሚው ፡ ምልክዮሽ ፡ እና ፡ ግብር ፡ ዐበሮቹ ፡ ይኾናሉ ፤ ተበዳዩ ፥ ርስቱን ፡ የተነጠቀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ... ።

**ጦርነቱ ፡ ባጪር ፡ እንዳይቋጭና ፡ ጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስያሳዊ ፡ ኹኔታ ፡ ተበለሻሽቶ ፥ እንደ ፡ ሶሪያ ፡ እና ፡ ሶማልያ ፥ መፍትሔ ፡ እንዲያጣ ፡ ይደረጋል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በማያባራ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ጦርነት ፡ ስትደማ ፥ ምልክዮሽ ፡ በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ ላይ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ምትክ ፥ ባለቤት- አልቦ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ተዳብሎ ፡ "confederation" ፡ የማዋቀር ፡ የከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ ዕቅዱን ፡ በመንደር ፡ ገነኖች ፡ ጭፍሮቹ ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድና ፡ ኢሳይያስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ አማካይነት ፡ ሊፈጽም ፡ ይሞክራል ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኹለቱን ፡ አገልጋዮቹን ፡ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ በ"ፀረ-ኢምፔሪያሊስት" ፡ አቋማቸው ፡ አበጃጅቶ ፡ ያስተዋውቃቸዋል ፤ በሌላ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ ከወርቅ ፡ ማዕድን ፡ እስከ ፡ ስኳር ፡ "ፋብሪካ" ፣ ከከተማ ፡ ቦታ ፡ እስከዕርሻ ፡ መሬት ፣ ከኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ እስከ ፡ ኢትዮቴሌኮም ፥ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይመነትፋቸዋል ። ሙሶሊኒ ፡ ባንድ ፡ ሚልዮን ፡ ሰራዊት ፡ ድል ፡ ያላደረጋትን ፡ ኢትዮጵያ ፥ ብልጡ ፡ ምልክዮሽ ፡ በጥቂት ፡ ከሃድያን ፡ መንደር ፡ ገነኖቹ ፡ አማካይነት ፡ ድል ፡ አደርጋታለኹ ፡ ብሎ ፡ ተማምኗል ። ኢትዮጵያ ፥ "ዐለቀላት!" ፡ ያሏትን ፡ ኹሉ ፥ "ዐለቀልን!" ፡ ያሠኘቻቸው ፡ መኾኗን ፡ እንዴት ፡ ዘነጋው ፧ ያውም ፡ የኮቪድ-19 ፡ ወረርሽኝ ፡ የዓለምን ፡ የኀይል ፡ ሚዛን ፡ እንዲህ ፡ በነቀነቀበት ፡ አደገኛ ፡ ወቅት ፡ ... ፧**

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ላንተ ፡ መንገር ፡ ለቀባሪው ፡ አረዱት ፡ ነው ። የገዛ ፡ ልጆችኽ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

እንደከዱኽ ፡ ካወቅኸው ፡ ከራርመኻል ። ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፥ *"ውሻ ፡ ወደ ፡ ትፋቱ ፡ ይመለሳል"* ፡ ሲል ፡ እንዳስተማረው ፥ ከሃዲዎች ፡ ልጆችኽ ፡ ወደ ፡ ትፋታቸው ፡ ተመልሰዋል ። ያጠፋኽን ፡ ባዕድ ፡ ተከል ፡ የ"አፓርትሀይድ" ፡ ሥርዐት ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ን ፡ እና ፡ ሕገ ፡ ውንብድናውን ፦ *"እናስቀጥላለን !"* ፡ ብለው ፡ ተማምለውብኻል ። ነገሩን ፡ በትዕግሥት ፡ እና ፡ በዘዴ ፡ ለመጨረስ ፡ ስታስታምመው ፡ ኖረኽ ፥ እንሆ ፡ ዛሬ ፥ ራሳቸው ፡ ለጥፋትኽ ፡ እቈሰቈሱት ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ አግብተውኽ ፥ እስካኹን ፡ ሲነጥቁኽ ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ታግለኽ ፡ ጨብጠኻል ።

የሥልጣን ፡ ባለቤት ፡ አንተ ፡ ነኽ ። በስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያልተቋረጠ ፡ የሥልጣኔ ፡ እና ፡ የነጻ ፡ ሕዝብነት ፣ የዐም ፡ ሐራነት ፡ ታሪክኽ ፥ ሥርዐተ ፡ መንግሥትኽን ፡ እየሠራኽና ፡ እያደስክ ፥ ዳር ፡ ድንበርኽን ፡ እያስከበርኽ ፥ መሪዎችኽን ፡ እየሾምክና ፡ እየሻርክ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ እግዚእናኽን ፡ አስፍነኽ ፡ ራስኽን ፡ በራስኽ ፡ ስትገዛ ፡ ኖረኻል ። ያለፉት ፡ ኀምሳ ፡ ዓመታት ፡ የቅርብ ፡ ጊዜ ፡ የውንብድና ፡ ታሪክ ፥ ጥንታዊውን ፡ እና ፡ ቋሚውን ፡ ሥልጡን ፡ ህልውናኽን ፡ ሊሠርዙት ፣ ርትዓዊ ፡ ኹነትኽን [4] ፡ ሊሽሩት ፣ ክቡር ፡ የነጻነት ፡ ታሪክኽን ፡ ሊያደብሱት ፡ አይችሉም ።

ዘላለማዊ ፡ የኾነውን ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነትኽን ፡ በዐዲስ ፡ ክዋኔ ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ መደንገግ ፥ በርሱም ፡ መሠረትነት ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥትኽን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማቆም ፡ ለማንም ፡ የማትተወው ፡ የወቅቱ ፡ የተቀደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥራኽ ፡ ኾኗል ።

ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ግን ፥ አንተም ፡ ታውቀዋለኽ ፥ አልቆለታል ። ከመሠረቱ ፥ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ሲያቋቁሙት ፥ ዐላማው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትባል ፡ ሀገርን ፡ አፈራርሶ ፥ ሀብቷን ፡ ለመቀራመት ፡ ነበር ። መኞት ፡ እና ፡ እውን ፡ እየቅል ፡ ናቸውና ፥ ውልቅልቁ ፡ የወጣው ፡ መሣሪያቸው ፡ ኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፥ እንሆ ፥ ራሱ ፡ እቈፈረው ፡ ጕድጓድ ፡ ቀድሞ ፡ ሊገባበት ፡ ይወጫመዳል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ እግዚእናኽን ፡ እንዳታስከብርና ፡ ዐዲሱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ እንዳትሠራ ፥ አንድነትኽም ፡ አካል ፡ እንዳያበጅና ፡ እንዳይቀናቀናቸው ፥ የምልክዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ እና ፡ መንደር ፡ ገነኞቹ ፡ ጭፍሮቻቸው ፥ በዘዴ ፡ በታትነውኽ ፡ ባዶኽን ፡ ሊያስቀሩኽ ፡ ዘወትር ፡ ይጠበባሉ ። በቅርቡ ፥ በዋሺንተን ፡ ከተማ ፡ *"የሽግግር ፡ መንግሥት ፡ መሥራቾች ፡ ነን"* ፡ ባዮች ፡ ባንዳዎቻቸውን ፡ ሰብስበው ፡ ያሳዩትን ፡ ተውኔት ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ማወራኛዎችና ፡ ደጋፊዎቻቸው ፡ ተቀባብለው ፡ ሲያስተጋቡትና ፡ ሲያጣጥሉት ፡ ታዝበኻል ። የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ዛሬ ፡ ከምትገኝበት ፡ ዐዘቅት ፡ ለማውጣት ፡ የሚያስችል ፡ አንድያው ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ነው ። መሸጋገሪያ ፡ መንግሥትን ፡ በክፉ ፡ ማንሣታቸው ፥ ፍቱን ፡ መድኀኒትነቱን ፡ ስላወቁት ፡ ነውና ፡ አትስማቸው ፤ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ዐብረን ፡ ሀገራችንን ፡ የምንፈወስበት ፡ መድኀኒት ፣ የምናሸጋግርበት ፡ ድልድይ ፡ ይኾነናል ።

**ዘመኑ ፡ ቀውጢ ፡ ኾኗል ። *"በቀውጢ ፡ ሰዓት ፡ ቀውጢ ፡ ኹን"* ፡ እንዳሉት ፡ የጥንት ፡ አባቶቹ ፥ ከእንግዲህ ፡ የሚያዋጣኽ ፥ የማይገታ ፡ እና ፡ የማይቀየስ ፡ የሕዝብ ፡ ማዕበል ፡ ኾነኽ ፡ ሀገርኽን ፡ መልሰኽ ፡ እእጅኽ ፡ እስክታስገባትና ፡ መንደር ፡ ገነኖችን ፡ ከጫንቃኽ ፡ እስክታሽቀነጥራቸው ፡ ድረስ ፥ በወያኔ ፡ መደምሰስ ፡ የውሸት ፡ ዜና ፡ ተዘናግተኽ ፡ ትጥቅኽን ፡ እንዳትፈታ ። በሦስቱ ፡ ቀለማት ፡ በአረንጓዴ ፣ ብጫ ፣ ቀይ ፡ በሚመሰለው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ዐላማኽ ፦**

- ***ሀገራዊ ፡ እግዚእናኽን ፡ ለማስከበር ፥***
- ***ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትኽን ፡ ለመሥራት ፥***
- ***ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥትኽን ፡ ለማቆም ፥***

**ትግልኽን ፡ በማዋሐድ ፣ በመደርጀትና ፡ በማጠናከር ፥ ሕዝባዊ ፡ ማዕበልኽን ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማኽ ፡ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ አዙረው ❖**

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ. ሀ ሥ አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net

---

4 **ኹነት ፡ (ወይም ፡ በግእዝ ፡ ኩነት)** ፤ የአካል ፡ ህላዌ ፥ እንነት ። በስያሳ/በአገዛዝ ፡ ትርጕሙ ፥ መንግሥት ፡ (State) ፡ ማለት ፡ ነው ። ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፥ በተሳሳተ ፡ አነጋገር ፥ "ኹነት"ን ፡ ድርስ ፡ (event) ፡ ለማለት ፡ ያውሉታል ፤ አይገባም ፥ ስሕተት ፡ ነው ። *"የወሳኝ ፡ ኩነት ፡ ምዝገባ ፡ ባለሥልጣን"* ፡ የተባለውም ፡ መንግሥታዊ ፡ ተቋም ፥ የልደት ፣ የጋብቻ ፣ የሞት ፡ ወዘተ. ፡ ድርሶችን ፡ ሲመዘግብ ፥ የሰዎችን ፡ ኹነት/ኩነት ፡ (ሲወለዱ ፡ ልጅነታቸውን ፣ ሲያገቡ ፡ ባለትዳርነታቸውን ፣ ሲሞቱ ፡ ሙትነታቸውን) ፡ ወስኖ ፡ ለመመዝገብና ፡ የምስክር ፡ ወረቀቱን ፡ ለሚመለከተው ፡ ለመስጠት ፡ የተቋቋመ ፡ እንጂ ፥ ድርስን ፡ ወይም ፡ ክንዋኔን ፡ ለመመዝገብ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ድርስ ፡ አካልን ፡ ለኩነት ፡ ያበቃዋል ፡ እንጂ ፥ ድርስ ፥ በራሱ ፥ ኩነትን ፡ አይኾንም ፥ የአካል ፡ ህላዌ ፡ የለውም ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።